# የአማራ ክልል መንግስት በቅማንት ጉዳይ የሰጠዉ ዉሳኔ
# ከህገ-መንግስት መስፈርቶች አንፃር ሲገመገም፤

የአንድ ማህበረሰብ የማንነት ጥያቄ የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች መብቶች መሠረትና ምንጭ በመሆኑ ከፍተኛ ግምት ሊሰጠዉ እንደሚገባ *የፌዴራሉ ህገ-መንግስት አጣሪ ጉባኤ* (Council of Constitutional Inquiry) የስልጤን ህዝብ የማንነት ጥያቄ ለመፍታት የህገ-መንግስት ትርጉም በሰጠበት ወቅት አፅንኦት ሰጥቷል፡፡ ስለሆነም የማንነትና የራስ በራስ ማስተዳደር ጥያቄ ባንድ ላይ በአንድ ማህበረሰብ ሲነሱ መጀመሪያ የማንነት ጥያቄዉ በግልፅ መመለስ አለበት፡፡ ማንነት የራስ አስተዳደር መሰረት ነዉ፡፡ ቋንቋ፣ባህልና ሃይማኖት የማንነት ዋና መገለጫዎች ናቸዉ፡፡

የቅማንት ህዝብ ከጥንት ጀምሮ ራሱን ከሌላዉ ህዝብ (ከአማራዉ) ለይቶ የሚያይበት የጎሳ ማንነት አለዉ (ethnic identity)፡፡ በአካባቢዉ የሚኖሩ የአማራ ጎሳ አባላትም የቅማንትን ህዝብ በጎሳ የተለዩ እንደሆኑ በማህበራዊም ሆነ በፖለቲካ እንቅስቃሲያቸዉ የሚያሳዩበት አረዳድና አቀባበል ጎልቶ ይታያል፡፡ ይህ በተለይ አድሎአዊ ተግባር ለመፈፀም ሲባል ቅማንቶችን በጎሳ ማንነታቸዉ ማግለል (an act of marginalization on the basis of their ethnic identity) የተለመደ ነዉ፡፡ በቅማንት ህዝብ ላይ ከድሮ ጀምሮ ስር ሰደዉ የቆዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮች በዋናነት በቅማንት የጎሳ ማንነት ላይ ያነጣጠሩ ናቸዉ፡፡ የቅማንት ህዝብ በከፍተኛ ደረጃ በኢኮኖሚ፣በፖለቲካ፣በማህበራዊና ባህላዊ ህይወቱ ላይ እየገጠመዉ ያለዉ አግላይና አድሎአዊ አስተዳደር (marginalizing and discriminatory administration) ዋና ምንጩ የጎሳ ማንነቱ (የቅማንት ማንነቱ) ከአማራዉ ህዝብ የተለየ መሆኑ ነዉ፡፡ ይህ ደግሞ በቀላሉ የማይጠፋና ልዩነቱ ታሪካዊ ይዘት ያለዉ ነዉ፡፡ የታሪክ ሰነዶች፣የጥናትና ምርምር ዉጤቶችና የታሪክ አባቶች እንደሚያስረዱት እስከ ደርግ ዘመነ መንግስት ድረስ በአማራና ቅማንት ጎሳዎች መካከል (በተለይም በሚኖሩባቸዉ ደንበር አካባቢዎች) ደም አፋሳሽ ግጭቶችና የንብረት ዘረፋ ድርጊቶች ይፈጠሩ እንደነበር ነዉ፡፡ አሁንም ቢሆን አልፎ አልፎ ጎሳን መሠረት ያደረጉ ግጭቶችና የንብረት ዘረፋ ወንጀሎች እንደሚከሰቱ ማሳያ ማስረጃዎች አሉ፡፡

አብላጫ ቁጥር ያለዉ የአማራ ህዝብ (Majority Amhara) በአንፃራዊነት አናሳ ቁጥር ያለዉን የቅማንት ህዝብ (Minority Kemant) ዉጦ በኃይል የማንነት ለዉጥ (forceful assimilation or forceful identity conversion) ለማምጣት ከጥንት አንስቶ እስከአሁኑ ዘመን ድረስ በመሪዎች አስተባባሪነት ስራዉ እየተሰራ ነዉ፡፡ ህዝቡን አስገድዶ በአማራ ጎሳ ስም በህዝብና ቤቶች ቆጠራ ወቅት እንዲቆጠር መደረጉ ለአብነት የሚጠቀስ ተግባር ነዉ፡፡ ይሁን እንጂ የቅማንት ጎሳ ልክ እንደ አማራ ጎሳ በስሙ በማንኛዉም መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋሞች መመዝገብና የጎሳ ማንነቱ እንዲታወቅለት ይፈልጋል፡፡ አማራም ሆነ ቅማንት መሆን ምርጫ እንጂ ግዳጅ የሚሆንበት ምንም ዓይነት ሳይንሳዊም ሆነ ህጋዊ ምክንያት የለምና፡፡

የአማራ ክልል መንግስት ያጠናዉን ጥናት መሠረት አድርጎ በቅማንት ጉዳይ ላይ ዉሳኔ ሲሰጥ **"ማንነት"** ላይ ትኩረት አልሰጠም ነበር፡፡ ትኩረት ያደረገዉ በማንነቱ መገለጫዎች (ቋንቋና ባህል) እና በራስ አስተዳደር ጥያቄዉ ላይ እንጅ የእነዚህ ሁሉ መሠረት ስለሆነዉ የቅማንት የጎሳ ማንነት (related ethnic identity) የክልሉ መንግስት ትኩረት አልሰጠም፡፡ በፌዴራሉ ህገ-መንግስት አንቀፅ 39(5) ስር እና በአብክመ የተሻሻለ ህገ-መንግስት አንቀፅ 39(7) ስር ከተቀመጡት የብሔረሰብ እዉቅና መስፈርቶች መካከል የህዝቦች በጋራ ወይም በተዛመደ ህልዉና (Related Identity) ማመናቸዉ ነዉ፡፡

ቅማንቶችን ከጥንት ጀምሮ በጋራ የሚያዛምዳቸዉ እና የጋራ ህልዉና አለን ብለዉ የሚያምኑበት የጎሳ ማንነታቸዉ (related ethnic identity) ነዉ፡፡ የቅማንት ህዝብ በጎሳ ማንነቱ ሳያፍርና ሳይሸማቀቅ በይፋ ታዉቆ መንቀሳቀስ ወይም እንደዜጋ መኖር ይሻል፡፡ በጎሳ ማንነቴ ስም ልቆጠር ልጠራ እንጅ በአማራ የጎሳ ማንነት ስም ልቆጠርና ልጠራ አይገባም በሚል እሰጥ አገባ ዉስጥ ይገኛል፡፡ በፌዴራሉ ህገ-መንግስት አንቀፅ 39(5) ስር እና በአብከመ የተሻሻለ ህገ-መንግስት አንቀፅ 39(7) ስር ከተቀመጡት የብሔረሰብ እዉቅና መስፈርቶች መካከል የጋራ የስነ ልቦና አንድነት (a common psychological make up) ሲሆን በቅማንት ህዝብ በኩል ይህ መስፈርት ባሁኑ ወቅት ጫፍ ላይ የደረሰ ነዉ፡፡ ለዚህ ማሳያዉ ደግሞ የቅማንት ህዝብ ከትልቅ እስከ ደቂቅ፣ ከምሁር እስከ አርሶ አደር

የክልሉ መንግስትም የቅማንት ህዝብ የተዛመደ ወይም የጋራ ህልዉና (related ethnic identity) አለኝ ብሎ እንደሚያምን የተስተዋለ መሆኑንና የጋራ የስነልቦና አንድነት (a common psychological make up) እንዳለዉ ማረጋገጡን ምክር ቤቱ በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ መረዳት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ የክልሉ መንግስት የቅማንትን የጎሳ ማንነት ልክ እንደሌሎች የህግ እዉቅና እንዳገኙ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የህግ እዉቅና (የአዋጅ እዉቅና) እንዲያገኝ የሚያስችል ዉሳኔ አልሰጠም ነበር፡፡ ይህ ከሆነ ዘንዳ አሁንም ቢሆን የቅማንት የማንነት ጉዳይ እንደድሮዉ ይፋ ሳይወጣ በሹክሹክታ ይቀጥላል ማለት ይሆናል፡፡ በህዝብ ቆጠራ ወቅት ቅማንት ብሎ መመዝገብ አይኖርም፡፡ ባጠቃላይ በመንግስት ተቋማትም ሆነ በግል ድርጅቶች በሚደረጉ ህጋዊ ዉጤት ባላቸዉ ምዝገባዎችና ሰነዶች ላይ የቅማንት ስም አይሰፍርም ማለት ነዉ፡፡ የአማራ ክልል መንግስት የቅማንት የጎሳ ማንነት እዉቅና (identity recognition) እንዲያገኝ ከጥንቱም ፍላጎት አልነበረዉም ማለት ይቻላል፡፡ ይፋ የሆነ ህጋዊ እዉቅና (official legal recognition) እስከሌለ ድረስ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ሚዲያዎችም ቢሆን የቅማንትን ጉዳይ በተመለከተ ሳይፈሩ ስሙን አንስተዉ መዘገብና ማሰራጨት አይችሉም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የክልሉ ምክር ቤት በቅማንት ጉዳይ ላይ ያስተላለፈዉ ዉሳኔ ሲገመገም የቅማንትን ማንነት አድበስብሶ አልፎታል ያሰኛል፡፡ የክልሉ መንግስት ቅማንት የሚባል ህዝብ ወይም ጎሳ የለም የሚል ዉሳኔ አላስተላለፈም፡፡ በእርግጥ የቅማንት ህዝብ ከጥንት ጀምሮ ኢትዮጵያ ዉስጥ የነበረ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ይሁን እንጂ ያለህግ እዉቅና (De Facto Recognition) እንደድሮዉ እንዲቀጥል ወስኗል፡፡ የቅማንት ማንነት የህግ እዉቅና (de jure recognition) ያስፈልገዋል፡፡ ስለማንነት አስፈላጊነት ጉዳይ የፌዴሬሽን ም/ቤት በስልጤ የማንነት ጉዳይ ላይ የሰጠዉን ዉሳኔ በጥልቀት መመልከቱ የቅማንትን ማንነት ጉዳይ ባግባቡ ለመመለስ ይረዳል፡፡

የክልሉ መንግስት ወይም ምክር ቤት የቅማንት የማንነት መገለጫዎች (kemant identity markers) ከሆኑት መካከል ቋንቋና ባህልን እንዲሁም ለራስ አስተዳደር ዋና መሠረት የሆነዉን የተያያዘ መልክዓ ምድር አሰፋፈር (contiguous territory) ከክልሉ ህገ-መንግስት አንቀፅ 39(7) ስር ከተቀመጡት የብሔረሰብነት መስፈርቶች አንፃር ወስዶ የተጣበበና የቅማንትን ህዝብ ጥቅም በከፍተኛ ደረጃ በሚጎዳ መንገድ የህገ-መንግስት ትርጉም በመስጠት ዉሳኔ አስተላልፏል፡፡ የእነዚህን መስፈርቶች አረዳድ በሚከተለዉ አግባብ ለማቅረብ እሞክራለሁ፤

## 1. ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ መኖር

በመጀመሪያ ደረጃ  አንድ ማህበረሰብ **"ብሔር ብሔረሰብ ወይም ህዝብ"** ለመባል **"ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ"** መኖር በፌዴራሉም (አንቀፅ 39(5)) ሆነ በአብክመ ህገ-መንግስት (አንቀፅ 39(7)) **እንደዋና ሳይሆን** እንደ አንድ መስፈርት ተቀምጧል፡፡ ሊያግባባ የሚችል የጋራ ቋንቋ ማለት ምን ማለት ነዉ? የሚለዉን ጥያቄ ወስደን የተለያየ ትርጉም ልንሰጥ እንችላለን፡፡ የሚከተሉትን ጥያቄዎችም ማንሳት እንችላለን፤

1) ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ማለት **የአፍ መፍቻ ቋንቋ** ብቻ ማለት ነዉ ወይስ **ሁለተኛ ቋንቋንም** ይጨምራል?
2) የአንድ ማህበረሰብ አባላት ስንት ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ሊኖራቸዉ ይችላል?
3) የአንድ ማህበረሰብ አባላት ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ አላቸዉ ስንል **ከሌላዉ ማህበረሰብ የተለየ የጋራ ቋንቋ** ይናገራሉ ማለታችን ነዉ ወይስ **ከሌላዉ ማህበረሰብ ጋር ተመሳሳይ የሆነ የጋራ ቋንቋ** ሊናገሩ ይችላሉ ማለታችን ነዉ?

ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ማለት የአንድን ማህበረሰብ አባላት በጋራ እስካግባባ ድረስ  የአፍ መፍቻ ቋንቋ ብቻ ሳይሆን ሁለተኛ ቋንቋም ሊሆን ይችላል፡፡ የቅማንት ህዝብ ባንድ ወቅት አማርኛ ቋንቋን በኃይልም ሆነ በፍላጎት ከመቀበሉ በፊት ሁሉም ቅማንትኛ ቋንቋን በአፍ መፍቻነት በጋራ ይግባቡበት እንደነበር ለመገመት አያዳግትም፡፡ ቅማንትኛ ቋንቋን በአፍ መፍቻነት ሲጠቀሙ ቆይተዉ አሁን ላይ ቋንቋዉን በሁለተኛ ቋንቋነት በደንብ በመናገር በጋራ የሚግባቡበት ዕድሜ ጠገብ ቅማንቶች ዛሬም ድረስ አሉ፡፡ በጥቅሉ ግን ባሁኑ ጊዜ አማርኛን ቋንቋ አቀላጥፎ የማይናገር ቅማንት አይገኝም፡፡ ስለሆነም አማርኛ ቋንቋ ቅማንቶች **"ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ"** ነዉ፡፡ ትናንት ላይ ሁነን ስንመለከት ቅማንትኛ ቋንቋ ቅማንቶች ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ነበር፡፡ ዛሬ ላይ ሁነን ስንመለከት ደግሞ አማርኛ ቋንቋ ቅማንቶች ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ሆኗል፡፡ ምናልባትም ነገ ላይ ሁነን ስንመለከት ቅማንትኛ ወይም አማርኛ ወይም ሁለቱም ቋንቋዎች ቅማንቶች ሊግባቡበት የሚችሉባቸዉ የጋራ ቋንቋዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ይህ ደግሞ የማንኛውም ቋንቋ አይነተኛ ባህርይ ነው፡፡

ምንም እንኳ የአብክመን የተሻሻለ ህገ-መንግስት የመተርጎም ስልጣን ያላቸዉ አካሎች የህገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ (The Council of Constitutional Inquiry) እና የህገ-መንግስት ተርጓሚ ኮሚሲዮን (The Commission for Constitutional Interpretation) ቢሆኑም (አብክመ ህገ-መንግስት አንቀፅ 71 እና 72) የአብክመ ምክር ቤት የክልሉ አስፈፃሚ አካል (ካቢኔ) እና የህግ ፍትህና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የሰጡትን ህገ-መንግስታዊ ትርጉም ወይም የዉሳኔ ሃሳብ መሠረት አድርጎ የቀረበዉ የቅማንት የማንነትና ራስ አስተዳደር ጥያቄ ህገ-መንግስቱ ያስቀመጠዉን የቋንቋ መስፈርት አያሟላም የሚል ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአንድ ማህበረሰብ አባላት **"ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ አላቸዉ"** ስንል የግድ ከሌላዉ ማህበረሰብ **የተለየ የጋራ ቋንቋ** ይናገራሉ ማለታችን አይደለም፤ ሊሆንም አይችልም፡፡  ከሌላዉ ማህበረሰብ ጋር **ተመሳሳይ የሆነ የጋራ ቋንቋ** ሊናገሩ ይችላሉ፡፡ ህገ-መንግስቱም **"ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ"** ያላቸዉ እንጂ **"ሊግባቡበት የሚችሉበት የተለየ የጋራ ቋንቋ ያላቸዉ"** አይልም፡፡ ከዚህ አንፃር ቅማንቶች ሁሉንም በጋራ የሚያግባባ ቅማንትኛ ቋንቋ እንዲኖራቸዉ አይጠበቅም፡፡ ይህ ሊሆን ይችል የነበረዉ ህገ-መንግስቱ **"ሊግባቡበት የሚችሉበት የተለየ የጋራ ቋንቋ ያላቸዉ"** በሚል የሚደነግግ ቢሆን

ነበር፡፡ ቅማንቶች ከአማርኛ ቋንቋ የተለየ በጋራ ሊግባቡበት የሚችሉበት ቅማንትኛ ቋንቋ ሊኖራቸዉ የግድ አያስፈልግም፡፡ ስለሆነም የክልሉ መንግስት ቅማንቶች የሚናገሩትን ቅማንትኛ ቋንቋ ያለበትንና የሚነገርበትን ደረጃ፣የሚነገርበትን ቦታ፣ የተናጋሪዎችን የዕድሜ ጣሪያና የተናጋሪዎችን ቁጥር ወስዶ የደረሰበት ድምዳሜ ከህገ-መንግስቱ መንፈስና ትርጉም ያፈነገጠ ነዉ፡፡ ከዚህ ላይ ሊጠቀስ የሚገባዉ ትልቅ ቁምነገር ቅማንቶች ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ አማርኛ ቋንቋ ቢሆንም ተገደዉ ካልሆነ በቀር ሁሉም ቅማንቶች ማለት ይቻላል **በቅማንት የጎሳ ማንነታቸዉ** (ethnic identity) ከአማራዉ ህዝብ ተለይተዉ እንደሚታወቁና ተለይተዉ መታወቅ እንደሚፈልጉ ነዉ፡፡

በሌላ መልኩ ግን ህገ-መንግስቱ **"ሊግባቡበት የሚችሉበት የተለየ የጋራ ቋንቋ ያላቸዉ"** በሚል የሚተረጎም ከሆነ ቅማንቶች የተለየ ማንነታቸዉ መገለጫ የሆነና በተፅዕኖ ምክንያት አደጋ ላይ የሚገኝ ቅማንትኛ የሚባል ቋንቋ አላቸዉ፡፡ ይህ ቋንቋ የተዳከመዉ በታሪክ አጋጣሚ በነበሩት አስከፊ ተፅዕኖዎች ምክንያት እንጂ በህዝቡ ነፃ ፍላጎት አይደለም፡፡ ቅማንቶች ይህን ቋንቋ መማር፣ማሳደግና ለመጭዉ ትዉልድ ማስተላለፍ ይፈልጋሉ፡፡ በመዳከሙም ቁጭታቸዉን ይገልፃሉ፡፡ ከ10,000 በላይ የሚገመት ቅማንትኛ ቋንቋ ተናጋሪ የቅማንት ህዝብ ሰፍሮ በሚገኝበት ክልል ዉስጥ ይኖራል፡፡ የክልሉ መንግስት ወይም ምክር ቤት ከሰጠዉ ዉሳኔ ለመረዳት እንደሚቻለዉ የቅማንት ህዝብ ቋንቋና ባህል በክልሉ መንግስት በኩል በጀት ተመድቦ እንዲጠበቁ እንደሚደረግ ዉሳኔ መተላለፉ የሚመሰገንና የሚደነቅ ቢሆንም ይህ ሲደረግ ግን **እንደአገር ሃብት ብቻ** ተወስዶ እንጂ የብሔረሰቡ **የማንነት መገለጫና ህገ-መንግስታዊ መብት** እንደሆነ ተቆጥሮ አይደለም፡፡ የቅማንትን ቋንቋና ባህል ከልብ ከመነጨ ተቆርቋሪነት እንደአገር ሃብት መጠበቅ ካስፈለገ በመጀመሪያ ደረጃ ባለቤቱ የሆነዉን ህዝብ ህገ-መንግስታዊ መብት ባግባቡ ማክበርና ማስከበር መቻል ያስፈልጋል፡፡ ባለቤት የሆነዉ የቅማንት ህዝብ የማንነትና ራስ አስተዳደር ህገ-መንግስታዊ ጥያቄ ባግባቡ ሳይመለስ አደጋ ላይ የሚገኘዉ ቋንቋም ሆነ ባህል ሊጠበቅና ሊያድግ አይችልም፡፡

ሁለተኛዉን ህገ-መንግስታዊ ትርጉም ተከትለን ሁሉም ቅማንቶች **"ሊግባቡበት የሚችሉበት የተለየ የጋራ ቋንቋ"** ሊኖራቸዉ ይገባል ብለን ብንከራከር እንኳ ሁሉም የብሄረሰቡ ተወላጆች ቋንቋዉን መቻል አለባቸዉ ብሎ መተርጎም የማይቻልባቸዉ ብዙ ምክኒያቶች አሉ፡-

- የመጀመሪያዉና ትልቁ ምክንያት ታሪካዊ ምክንያት ነዉ፡፡ ባለፉት የኢትዮጵያ መንግስታት ታሪክ አማርኛ ቋንቋ በሌሎች ቋንቋዎች ላይ ነግሶ አብዛኛዎቹን ማጥፋቱና ማዳከሙ የማይካድ ሃቅ ነዉ፡፡ በተለይም በአማራ ክልል ዉስጥ በሚገኙት የአገዉ ቋንቋዎች ላይ አማርኛ ቋንቋ ያደረሰዉ ተፅዕኖ ቀላል አይባልም፡፡ የቅማንትኛ ቋንቋም አንዱ ገፈት ቀማሽ ነዉ፡፡ ይህ ታሪካዊ እዉነታ እያለ ሙሉ በሙሉ ቋንቋ ተናጋሪ ቅማንት ይኖራል ብሎ መነሳት ትልቅ የትርጉም ስህተት ነዉ፡፡ ህገ-መንግስቱም ሲረቀቅ ይህን እዉነታ ግምት ዉስጥ በማስገባት **"ሁሉም የማህበረሰቡ አባላት ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸዉ"** ብሎ አልተነሳም፤
- ይህንን ሃቅ መሠረት በማድረግም በአማራ ክልል ዉስጥ የማንነትና ራስ አስተዳደር እዉቅና የተሰጣቸዉ ሁሉም ብሄረሰቦች ማለት ይቻላል ሙሉ በሙሉ ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ተናጋሪ ህዝብ አልነበራቸዉም፡፡ ሁሉም ቢሆን በአማርኛ ቋንቋ ከባድ ተፅዕኖ ስር የነበሩ ቋንቋዎች ነበሯቸዉ፡፡ ህገ-መንግስታዊ ወይም ህጋዊ እዉቅና ካገኙ በኋላ ባገኙት ነፃነት ተጠቅመዉ በሞት ላይ የሚገኙትን ቋንቋዎቻቸዉን እንደገና እንዲያንሰራሩ አድርገዋል፡፡ አሁንም ድረስ አገዉኛ ቋንቋ የማይናገሩ የዋገኽምራ ብሔረሰብ ዞን ወረዳዎች (ለምሳሌ ዳሃና ወረዳ) ይገኛሉ፡፡ የአገዉ አዊን ጉዳይም ብንመለከት ተመሳሳይ ነገር እናገኛለን፡፡ ዳንግላ ወረዳን እንደምሳሌ ወስደን

ብንመለከት እስካሁን ድረስ ከአዉኛ ቋንቋ ይልቅ አማርኛ ቋንቋ የሚነገርበት ወረዳ ነዉ፡፡ አንዳንዶቹ ብሄረሰቦችና ክልሎች እስካሁንም ድረስ የስራ ቋንቋቸዉ አማርኛ ነዉ፡፡ ይህ ሁኔታ ራሳቸዉን በራሳቸዉ ከማስተዳደር ያገዳቸዉ ምንም ነገር የለም፡፡ ሊኖርም አይገባም፡፡ የስልጤ የማንነት ጉዳይ ዉሳኔ ባገኘበት ወቅትም ተመሳሳይ የሆነ የጉራግኛ ቋንቋ ተፅዕኖ ነበር፡፡ ከሁሉ በላይ ግን የአብክመ ምክር ቤት ካሁን በፊት ዉሳኔ ያስተላለፈበትን የአርጎባን ብሔረሰብ ቋንቋ ያለበትን ሁኔታ ማየት የቅማንትን የማንነትና ራስ አስተዳደር ጥያቄ ለመመለስ ብዙ ማሰብ አይጠይቅም ነበር፡፡ የአርጎባ ብሔረሰብ ካላቸዉ የህዝብ ቁጥር (37, 000 ህዝብ በላይ) መካከል 12,000 አካባቢ ቋንቋ ተናጋሪ ብቻ አላቸዉ (በ1999 የተደረገዉን የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ዉጤት መመልከት ይቻላል)፡፡ የእነዚህ ቋንቋ ተናጋሪዎች አሰፋፈርም እዚህና እዚያ ነዉ፡፡ አንድ አካባቢ ኩችች ብለዉ በኩታ ገጠምነት አይኖሩም፡፡ የቋንቋዉ ተናጋሪዎችም ዕድሜ ጠገቦች ናቸዉ፤

- ከሁሉም በላይ ግን ወሳኙ የህዝቡ ፍላጎትና ዉሳኔ ነዉ፡፡ ማንኛዉም የማንነትና ራስ አስተዳደር ጥያቄ መጨረሻ ላይ ምላሽ የሚያገኘዉ በህዝቡ ፍላጎትና ዉሳኔ ነዉ፡፡ የስልጤን የማንነትና ራስ አሳተዳደር ጥያቄን ተከትሎም ህዝበ ዉሳኔ የመጨረሻዉ መፍትሔ አማራጭና ህዝቡም መብቱን የሚያረጋግጥበት ህገ-መግስታዊ መንገድ እንደሆነ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ህገ-መንግስቱን በተረጎመበት ወቅት አረጋግጧል፡፡ ይህ እዉነታም በህገ-መንግስቱ ዉስጥ ወሳኝ መርህ ሆኖ ተደንግጓል፡፡ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ብሄረሰቦች፣ ህዝቦች የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤቶች ናቸዉ፡፡ ህገ-መንግስቱም የሉዓላዊነታቸዉ መገለጫ ነዉ፡፡ ሉዓላዊነታቸዉም የሚገለፀዉ በህገ-መንግስቱ መሠረት በሚመርጧቸዉ ተወካዮቻቸዉና ቀጥታ በሚያደርጉት ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ አማካይነት ይሆናል (አንቀፅ 8) ፡፡ ህዝበ ዉሳኔ ህዝቦች በቀጥታ ከሚሳተፉባቸዉ መንገዶች አንዱና ወሳኙ ነዉ፡፡ ስለሆነም የቅማንት የማንነትና ራስ አስተዳደር ጥያቄ በተወካዮቹ (የፌዴራል መንግስትና የክልል መንግስት) አማካይነት ፍትሃዊ መፍትሔ ካላገኘ በህዝቡ ዉሳኔ የመጨረሻ መፍትሔ ሊያገኝ እንደሚችልና ህዝበ ዉሳኔም ህገ-መንግስታዊ መብት መሆኑ ለማንም ግልፅ ነዉ፡፡

### 2. ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንፀባርቅ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች መኖር

በሁለተኛ ደረጃ በፌደራሉም ሆነ በአብክመ ህገ-መንግስት መሠረት የብሔረሰብነት እዉቅና ለማግኘት አንድ ማህበረሰብ **"ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንፀባርቅ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች"** እንዲኖሩት ያስፈልጋል፡፡ ልክ ከዚህ በላይ ቋንቋን እንደመስፈርት ባየንበት መንገድ **"ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንፀባርቅ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች"** ያላቸዉ ማለት **ከሌላዉ ማህበረሰብ ልዩ የሚያደርጋቸዉ** ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚንፀባርቅ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸዉ ማለትን አያመለክትም፡፡ በቅማንትና አማራ መካከል ጎልቶ የወጣ የተለየ ባህል የግድ አስፈላጊ አይደለም፡፡ ህገ-መንግስቱ በግልፅ እንደዚያ ብሎ አያስቀምጥምና፡፡

ሃይማኖትና ቋንቋ አንድ ማህበረሰብ ለሚያዳብረዉ ባህል ትልቅ ድርሻ አላቸዉ፡፡ የቅማንት ህዝብ ተገዶ የክርስትናን እምነት እንዲቀበል ሲደረግ ልክ እንደ አማራዉ ህዝብ ተመሳሳይ ክርስቲያናዊ ይዘት ያላቸዉ ባህሎች ወይም ልምዶች መቀበሉ አልቀረም፡፡ በዚህ በኩል ተወራራሽ ባህል ወይም ተመሳሳይ ባህል  ሊኖር ይችላል፡፡ ይህ እንዳለ ሁኖ ግን አሁንም ድረስ በቅማንት ማህበረሰብ ዉስጥ ከጥንት ጀምረዉ የቆዩ ቱባ ባህሎች አሉ፡፡ ዋናዉ ቁም ነገር ጥልቅና ሳይንሳዊ ጥናቶች አለመኖራቸዉ ነዉ፡፡ የቅማንት የማንነትና ራስ አስተዳደር ጥያቄ አስተባባሪ ኮሚቴ በቂ ጊዜ የፈጀ ጥልቅ ጥናት አስጠንቶ

ለመቅረብ የክልሉን መንግስት በጀት ቢጠይቅም ሊሳካለት አልቻለም፡፡ የቆየዉን **የቅማንት ህገ-ልቦና ሃይማኖት** ብቻ ወስደን ብንመለከት እንኳ ቅማንትን ከሌላዉ ማህበረሰብ በእጅጉ የሚለዩ ባህሎችን ነቅሰን ማዉጣት እንችላለን፡፡ ካሁን ቀደምም የክልሉ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ቢሮም ሆነ የሰሜን ጎንደር ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ባዘጋጇቸዉ የባህል ዉድድር መድረኮች የቅማንትን ባህል ወክለዉ የቀረቡት የህገ-ልቦና ቄሶች (ከመዘናዎች) ብዙ ጊዜ አሸናፊ ሆነዋል፡፡ የፌዴራል ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በበኩሉም ያስጠናዉና የዘገበዉ መረጃ አለ፡፡

ከዚህ ላይ ሊጠቀስ የሚገባዉ ትልቁ ችግር የቅማንት ህገ-ልቦና ሃይማኖት በዉስጡ የያዘዉ ባህልና ትዉፊት ስለሚታወቅ ይህን ሃይማኖት ለማጥፋት የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ቤተክርስቲያን ከጥንት ጀምራ እስከአሁን ድረስ የማትፈነቅለዉ ድንጋይ የለም፡፡ ሌላዉ ቀርቶ የክልሉ መንግስት ወይም ምክር ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ በጣም ጥቂት ግለሰቦች የሆኑ የሃይማኖቱ ተከታዮች የሚከተሉት ሃይማኖት ነዉ መባሉ ትክክል አይደለም፡፡ ከ300 በላይ የሚገመት የሃይማኖቱ ተከታዮች በጭልጋ ወረዳ እንደሚገኙ የክልሉ መንግስት ራሱ የመዘገበዉ ሰነድ ያስረዳል፡፡ የቅማንት ህገ-ልቦና ሃይማኖትና የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ተመሳሳይነት እንዳላቸዉ የክልሉ ምክር ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ መገለፁም መሠረታዊ የፍሬ ነገር ስህተት ( factual error) ያለበት ነዉ፡፡ እነዚህ ሃይማኖቶች ተመሳሳይነት ቢኖራቸዉ ኑሮ ከጥንት ጀምሮ በሁለቱ ሃይማኖቶች መካከል ቅራኔ (contradiction) ባልኖረ ነበር፡፡ ይህ ተፅዕኖ ባለበት ሁኔታ ከአማራዉ ጎልቶ የተለየ የቅማንት ባህል ማግኘት ቀልድ ከመሆን አይዘልም፡፡

ሌላዉ ሊነሳ የሚችለዉ ጥያቄ ወደ ክርክር ዉስጥ ይገባ ከተባለ ሰ/ጎንደር ላይ የሚንፀባረቀዉ ባህል የማን ነዉ? የቀደምት ነዋሪዉ የቅማንት ህዝብ ወይስ የአማራዉ? ማን ከማን ወሰደ? የሚለዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ ይህም ራሱ ገለልተኛና ሳይንሳዊ ጥናት የሚያስፈልገዉ ነገር ነዉ፡፡ በአጠቃላይ ከቅማንት ህዝብ ፍላጎት ዉጭ ከጥንት ጀምሮ በመንግስት የተደገፈ የማንነት ማጥፋት ወይም ዉህደት (government-sponsored identity destruction or forceful assimilation through Amharization process) ስራ ከተለያየ አቅጣጫ ተጠናክሮ በቀጠለበት ጎን ለጎን ከአማራዉ ጎልቶ የወጣ ባህል አምጡ ማለት ፍትሃዊና የነፃነት መርህን የተከተለ አይደለም፡፡

### 3. ባብዛኛዉ በተያያዘ መልከዓ ምድር መኖር

በሶስተኛ ደረጃ በፌዴራሉ ህገ-መንግስትም ሆነ በአብክመ የተሻሻለ ህገ-መንግስት መሠረት አንድ ማህበተሰብ የብሄረሰብነት እዉቅና ለማግኘት የማህበረሰቡ አባላት **"ባብዛኛዉ በተያያዘ መልከዓ ምድር የሚኖሩ"** መሆን አለባቸዉ፡፡ ይህ መስፈርት በተለይ በታሪክ ግፍና በደል ለሚደርስባቸዉ አናሳ ብሔረሰቦች ወይም ህዝቦች (Minority Nationalities or Peoples) የራስ አስተዳደር ለመፍቀድ እጅግ ጠቃሚና አስፈላጊ ህገ-መንግስታዊ መስፈርት ነዉ፡፡ የማህበረሰቡ አባላት **"ሙሉ በሙሉ በተያያዘ መልከዓ ምድር"** እንዲኖሩ አይጠበቅም፡፡ **"ባብዛኛዉ"** የሚለዉ ቃል ይህንን ያመለክታል፡፡ በግምት **95%** የሚሆነዉ የቅማንት ህዝብ በተያያዘ እና በኩታ ገጠምነት ሰፍሮ ይገኛል ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ በዘር ግንድ ቅማንት ነኝ ብሎ የሚያምነዉ ህዝብ ከአማራ ህዝብ ጋር ሳይቀላቀል (ከወገራ ወረዳ የተወሰኑ ቀበሌዎች ጀምሮ እስከ ቋራ ወረዳ የተወሰኑ ቀበሌዎች ድረስ) ከላይ በግምት በተገለፀዉ መጠን ኩታ ገጠም በሆነ መንገድ ሰፍሮ ይገኛል፡፡ ይሁን እንጂ የአማራ ክልል መንግስት ወይም ምክር ቤት **የቅማንትኛ ቋንቋ ተናጋሪንና ኩታ ገጠም አሰፋፈር** ግምት ዉስጥ አስገብቶ ህገ-መንግስቱ ከሚለዉ ዉጭ የቅማንት ህዝብ የራስ አስተዳደር መብት አይገባዉም ብሎ መወሰኑ አግባብነት የለዉም፡፡ እንደዚህ ዓይነት የህገ-መንግስት ትርጉም በታሪክ ከፍተኛ ጭቆና የደረሰባቸዉንና እየደረሰባቸዉ የሚገኙትን እንደቅማንት

ያሉትን አናሳ ብሄረሰቦች ወይም ህዝቦች መብት የሚጎዳ በመሆኑ ህገ-መንግስቱ ሲተረጎም በጠባቡ ሳይሆን በሰፊዉ (broad and effective constitutional interpretation) መተርጎም ይኖርበታል፡፡

የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን (International Covenant on Civil and Political Rights) እንደሚደነግገዉ በጎሳ፣በሃይማኖት ወይም በቋንቋ አናሳ የሆኑ ማህበረሰቦች ባሉበት አገር ዉስጥ የአናሳ ማህበረሰቡ አባል የሆኑ ግለሰቦች **በጋራ** ባህላቸዉን እንዳያከብሩ፣ሃይማኖታቸዉን እንዳያስፋፉ ወይም በቋንቋቸዉ እንዳይጠቀሙ መብታቸዉ ሊገፈፍ አይገባም (አንቀፅ 27)፡፡ የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብት ኮሚቴ (UN Human Rights Committee) ከላይ የተጠቀሰዉን አንቀፅ እንደተረጎመዉ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን ሰነድ ፈራሚ አባል አገሮች በጎሳ፣በሃይማኖት ወይም በቋንቋ አናሳ የሆኑ ማህበረሰቦችን መሠረታዊ መብቶች ማክበርና ማስከበር እንዳለባቸዉ ነዉ፡፡ ኢትዮጵያ አገራችንም የዚህ ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን ሰነድ ፈራሚ አገር እንደመሆኗ መጠን በፌዴራሉ ህገ-መንግስት አንቀፅ 39(5) እና በአብክመ የተሻሻለ ህገ-መንግስት አንቀፅ 39(7) ስር የተቀመጡት የብሔረሰብነት መስፈርቶች ሲተረጎሙ የአናሳ ብሄረሰቦችን ወይም ህዝቦችን መሠረታዊ ሰብአዊ መብቶች በሚያሳንስና በሚያጣብ መንገድ መሆን አይገባዉም፡፡ በህገ-መንግስቱ ዉስጥ የተካተቱት መሠረታዊ የመብቶችና ነፃነቶች (የብሄር ብሄረሰቦችንና ህዝቦችን መብት ጨምሮ) ድንጋጌዎች ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸዉ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ህግጋት፣ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችና ዓለም አቀፍ ሰነዶች መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ መተርጎም እንዳለባቸዉ የፌዴራሉ ህገ-መንግስት አንቀፅ 13(2) ይደነግጋል፡፡

በአጠቃላይ እስካሁን ድረስ ካደረግናቸዉ ገለፃዎች መረዳት እንደምንችለዉ የቅማንት የማንነትና ራስ አስተዳደር ህገ-መንግስታዊ ጥያቄ የማይመለስበት አጥጋቢ ህጋዊ ምክንያት አለመኖሩን ነዉ፤ የቀረበዉን ጥያቄም ለመመለስ የክልሉ መንግስት ከህጋዊነት አግባብ ወጥቶ የፖለቲካ መፍትሄ አማራጭ ዉስጥ መግባቱም አግባብነት የለዉም፡፡

ከጥላሁን ጀምበር

ነሐሴ 2007